# በርግጥ እምነት ምንድን ነው?

*ከተስፋዬ ሮበሌ*

## መግቢያ

በሰባዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የኮሪያዊው ሰባኪ የፖል ዮንጊ ቾ[1] ስብከቶች በካሴት ተዘጋጅተው በአገሪቱ ውስጥ በስፋት ይሠራጩና ይደመጡ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። በተለይ፣ "ዘ ፎርዝ ዳይሜንሽን" ("The Fourth Dimension, Vol. 1 and Vol. 2")[2] በሚል ርእስ የታተሙት ሁለት ቅጽ መጻሕፍት፣ ብዙዎች እጹብ ድንቅ በማለት አሞካሽተውት ነበር[3]። ከሊቅ እስከ ደቂቅ በትምህርቱ ያልተደመመ፣ ከአምላክ ማደሪያ/ጸባኦት በቀጥታ የተቀዳ መገለጥ መሆኑን ያላጸደቀ ግለሰብ ያለ አይመስለኝም[4]። የዐቅብተ እምነት አገልግሎት ብቻ ሳይሆን፣ ነገር መለኮትም በቅጡ በማይታወቅበት በዚያ ጨለማ ዘመን፣ አለማወቅን ተገን አድርጎ የተነሣው ይህ ትምህርት፣ አላንዳች ከልካይ እንደ ተዛማጅ በሽታ አገሪቱ ላይ ናኘቶአል፤ የቤተ ክርስቲያንንም አስተምህሮና ሥነ ምግባር ክፉኛ በርዟል።

ከመነሻው የብዙዎችን ልብ የሳበው ይህ ትምህርት፣ ከሱ በኋላ ለመጡት መሰል "የእምነት እንቅስቃሴ" ትምህርቶች[5] ትልቅ የማደላደል ሥራ ሠርቷል። የእንቅስቃሴው ልሳን የነበረውና

---

[1] ኋላ፣ "አምላክ ስሜን እንድቀይር አዞኛል" ካለበት ጊዜ ጀምሮ፣ ዴቪድ ተብሎ ይጠራል። ታክስ በማጭበርበር እንዲሁም የቤተ ክርቲያኒቱን ገንዘብ ሃያ (ሚሊዮን ዶላር) ለራሱ ጥቅም በማዋል በተደጋጋሚ ክስ ቀርቦበታል። እንደ ጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር የካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ታክስ በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ ለሦስት ዓመት ዘብጥያ ተወርውሯል። ከእስራት ቅጣቱም በተጨማሪ አምስት ሚሊዮን ዶላር መቀጫ እንዲከፍል ተበይኖበታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የበኵር ልጁ ከአባቱ ጋር አባሪ ተባባሪ በመሆኑ ምክንያት የሦስት ዓመት የእስር ቅጣት ተጥሎበታል። የተለያዩ ምንጮች ግለሰቡ በካሄደው ወንጀል መጸጸቱን ዘግበዋል። የዚህን መረጃ እውነተኛነት፣ "ዘኢኮኖሚስት"፣ "ክርስቲያኒቲ ቱደይ" እንዲሁም "ጎስፐል ሄራልድ" ማረጋገጥ ይቻላል። ምንጮቹ እነሆ:— *The Economist* 15 October 2011

http://www.gospelherald.com/articles/50492/20140224/david-yonggi-cho-reflects-on-guilty-verdict-hardest-day-of-50-years-of-ministry.htm#ixzz3NKvvPnz4

http://www.christianitytoday.com/gleanings/2014/february/founder-of-worlds-largest-megachurch-convicted-cho-yoido.html

[2] David Yonggi Cho (1979), *The Fourth Dimension (Vol. 1): Discovering A New World of Answered Prayer,* (Bridge-Logos, Alachua, FL, USA). David Yonggi Cho (1983), *The Fourth Dimension (Vol. 2): More Secrets for a Successful Faith Life* (Bridge-Logos, Alachua, FL, USA).

[3] እኔ በበኩሌ ኑፋቄ እየኰመኰምን ማደጋችንን ያስተዋልሁት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከገባሁ በኋላ ነው።

[4] እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ትምህርቱ ስሕተት እንደ ሆነ በተደራጀ መንገድ ይፋ ያደረጉት፣ የቤዛ ባፕቲስቶቹ ለዐከ ታፈሰና ፍሥሓ ደጀኔ ናቸው። ኋላ ግን በርካታ ሰዎች ትምህርቱ ስሕተት ነው ሲሉ ሞግተዋል፤ ለምሳሌ የሙሉ ወንጌሉ ወንድም ተሾመ ነጋሽ፣ የመካነ ኢየሱሱ ዶ/ር ሽመልስ አድማሴ፣ የቃለ ሕይወቱ ግርማዊ ቡሹ። ኋላ ማለትም በሰማንያዎቹ መጀመሪያ ላይ፣ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ባዘጋጀው ዐውደ ጥናት ላይ፣ እኔን ጨምሮ የመሠረተ ክርስቶሶቹ ወንድም ሰሎሞን ከበደና ወንድም ሰሎሞን ጥላሁን እንዲሁም ዶ/ር ሽማልስ አድማሴ በትምህርቱ ስሑትነት ላይ ሒስ ሰንዝረናል።

[5] ምንም እንኳ ቾ ትምህርቱን በቀጥታ ያገኘው፣ አምላክ በጸሎት ጊዜው እየመጣ ከሚናገረው ንግግር እንደ ሆነ ቢገልጽም፣ ከእነዚህ በርካታ መገለጦች በኋላ፣ ለተባለው ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ እንዳገኘ ቢያስረዳም፣ ማኮኔል የተባለው አሜሪካዊ ጸሓፊ፣ ዲቪድ ዮንጊ ቾ ይህን ትምህርት በቀጥታ የቀዳው ከእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ማለትም ከኢ ደብሊው ኬኒየንና ከኬኔት ሐጊን እንደ ሆነ በማስረጃ ሞግቷል። D.R. McConnell (1988,

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ታትሞ በአገሪቱ ውስጥ በስፋት ይሠራጭ የነበረው "አክትስ" መጽሔት፣ ለእንቅስቃሴው ማበብ ትልቅ ድርሻ ነበረው፡፡ ኋላ በእንቅስቃሴው አስተምህሮ የደቀኑ የናይጄሪያ ሰባኪያን ወደ አገሪቱ በስፋት በመግባት፣ በጽሑፍና በካሴት የተሠራጨውን መከር በጥቂት ወራት መሰብሰብ ችለዋል፡፡ ምናልባት ትምህርቱ ሞተ ሲባል ዐፈር እያላሰ የሚነሣው፣ ከተገመተው በላይ ሥር ስለሰደደ ይሆንን? እኔ በዚህ ጽሑፍ ይህ እንቅስቃሴ እምነትነትን አስመልክቶ የሚያስተምረውን ትምህርት እተቻለሁ፡፡

## እምነት

ክርስትና ድሩም ማጉም እምነት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ማመን፤ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፤ በመንፈስ ቅዱስ ማመን፣ በሙታን ትንሣኤ ማመን፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ግብር ማመን ወዘተረፈ፡፡ በአጠቃላይ ክርስትና ዋልታና ማገሩ፣ መሠረቱና ውቅሩ እምነት ነው፡፡ የቃሉን ትርጓሜና ዳር ድንበር፣ የመሠረተ ሐሳቡን ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም በርእሰ ጉዳዩ ላይ በሚቀርቡ መስመር የሳቱ ትምህርቶችና ልምምዶች ላይ ሒስ መሰንዘር፣ የዚህ ጽሑፍ መነሻም መድረሻም ነው፡፡ በአጭሩ ጽሑፉ ትምህርታዊና ዐቅብተ እምነታዊ ተልእኮ በመሰነቅ፣ ቃለ እግዚአብሔርንና ምክንዩን የጉዞ መስመሩ ያረገ ድርሳን ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንዳንድ የሃይማኖት መምህራን፣ እምነት ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጓሜ እንዲሁም ለትርጓሜያቸው የቀመሩት ነባቤ ቃል፣ ግዘፍ ነሥቶ ገቢራዊ እንዲሆን የሚያደርጓቸው ጥረቶች፣ ክርስቲያናዊ ያለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ብዙ ዝርክርክ ነገር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል እየሆነም ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ጌታን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ከተቀበልሁበት ዘመን ጀምሮ፣ ቤተ ክርስቲያን በብዙ እንግዳ ደራሽ ትምህርቶች ስትናጥ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ላልሆኑ ልምምዶች ሰለባ ስንሆን አይቻለሁ፡፡ ነገር ግን የእምነት እንቅስቃሴ እንደሚባለው ወልካፋ ትምህርት በቤተ ክርስቲያንን ያስነወረ፣ ከፍተኛም ውድመት ያመጣ ስሑት አስተምህሮ ያለ አይመስለኝም፡፡ "በዚህ ትምህርት የተነካካው ማነው?" ከሚለው ምርመራ ይልቅ፣ "ያልተነካካው ማነው?" የሚለው ጥረት ከብዙ አንጻር ድካምን የሚቀንስ ይመስለኛል፡፡ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለትምህርቱ ሎሌ አድሯል፡፡ ይህ አነጋገሬ እውነት ከሆነ ይህ ጽሑፍ ወቅታዊ እንዲሁም በአንገብጋቢ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሒስ የሚሰነዝር ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ ሚዛናዊናት የጐደለው ምናልባትም የተሳሳተ ነገር ብታገኙ ማቅማማት እንድታሳውቁኝ በጌታ ፍቅር እጠይቃለሁ፣ "ሰው ሆኖ አይስት እንጨት ሆኖ አይጥስ" የለምና፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ጽሑፎችም ቀዳማይ ዐላማቸው ይኸው ነው[6]፡፡

## ሐተታ

ሰንበት ትምህርት ቤት ውሎ የመጣ ወጣት እናቱ፣ "ልጄ ዛሬ ምን ተማራችሁ" ብላ ስትጠይቀው፣ "ስለ እምነት፤ ዛሬ የተማርነው ስለ እምነት ነው" ይላታል፡፡ "ስለ እምነት ምን ተማራችሁ"፣ "እምነት እንደማይሆን የተረጋገጠን ነገር ፈጽሞ ጨልጦ ማመን ነው፤ እንዲያውም

---

1995, 2007), *A Different Gospel (Updated Edition): A Bold and Revealing Look at the Biblical and Historical Basis of the Word of Faith Movement* (Hendrickson Publishers, Peabody, MA, USA).

[6] ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በአማሪካኗ በሜሪላንድ ክፍለ አገር ኦገስት 7 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገ ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ ጽሑፍ ነው፡፡ ወንድም ሚኪያስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካቶ ብዙዎች እንዲያነቡት በማድረጉ ላመሰግነው እወዳለሁ፡፡ እግዚአብሔር አምላክ አገልግሎትህንም ሆነ ሕይወትህን አትረፍርፎ ይባርክ፡፡

ትክክል እንዳልሆነ የተረጋገጠውን ይህ ዐይነቱን ነገር ፍርጥም ብሎ ያለማመን ጥርጣሬና ምንታዌ ነው" እንዳለ አንብብያለሁ—ግነትና ድምቀት መጨመሬን ግን አልክድም። በተመሳሳይ መልኩ፣ አንድ የወጣት መሪ፣ "እኔ እግዚአብሔር ብሆን ኖሮ ነገሮችን ሁሉ ፍጹም ግልጽ በማድረግ፣ እምነት በሕይወታችን ውስጥ አንዳችም ፋይዳ እንዳይኖረው አደርግ ነበር" ማለቱ ትዝ ይለኛል። አንድ የእምነት እንቅስቃሴ መምህር ደግሞ፣ እምነት የሚለውን ቃል የተረጓመው በሚከተለው መልክ ነው፣ "እምነት ማለት ጉዳዩ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሶ ባይገኝ ኖሮ፣ ቀልቡን ያልሳተ ጤናማ ሰው ሊሆን ይችላል ብሎ በጭራሽ የማይቀበለውን ነገር አምኖ መገኘት ነው"።

በቨርጅኒያ አካባቢ የሚኖሩ፣ "እኔ የእምነት እንቅስቃሴ መምህር ነኝ"[7]፣ "እኔ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪ ነኝ"[8] እያሉ በግልጽ የሚናገሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ሰባኪ፣ "ራይዝ ኤንድ ሻይን" በተባለ ቶክ ሾ ላይ ቀርበው እንዲህ ብለዋል፣ "ፋክትና ሪያሊቲ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ትምህርት ሁሉ ሪያሊቲ ነው። ኢየሱስ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት ሲያስነሣ፣ ተኝታለች ነው ያለው፤ ይህም ኢየሱስ ሞታለች የሚለውን ክዶታል። ተኝታለች ብሎ በመናገሩ ሪያሊቲውን ስለካደ ልጅቱ አልሞተችም፤ ነገር ግን ተኝታለች። ስለዚህ ኢየሱስ የሞተውን ሰው ሳይሆን ያስነሣው ያንቀላፋውን ሰው ነው"[9]።

እስካሁን ያየናቸው የእምነት ትንታኔዎች ትክክል ከሆኑ፣ እምነት እውር ድንብሩ የወጣ፣ ደመናፍሳውያኑ እንስሳት እንጂ አእምሮ የተቸረው ፍጥረት የማይቀበለው፣ የወይዛዝርት ዋዛ ፈዛዛ ነው። አእምሮ ያለው ፍጥረት አእምሮ ቢስ ለመሆን ሲዳዳ፣ በምክንያትነት የሚያቀርበው ሰበብ (ተገን) ነው ማለት ነው። በርግጥ እምነት ማለት እነዚህ ሰዎች ያሉት ነገር ከሆነ፣ እምነት አሻሚ እንዲያውም ከምክንዩ ጋር ተጻራሪ የሆኑ ነገሮችን ለመቀበል በምክንያትነት የምናጣቅሰው የጥንቈላ ብትር ነው ማለት ነው። ስለዚህ አንድ ነገር እምነት ፈለገ ማለት ነገሩ አሻሚ ነው ወይም ነገሩን ለመቀበል አንዳችም እእምሮአዊ ማስረጃ የለም ማለት ነው።

ይህ ጽሑፍ በሁለት መሠረታውያን ነገሮችን ይመረምራል:—

1. እምነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ስለ እምነት የሚሰጠው ትንታኔ በቅዱሳት መጻሕፍት ሲፈተሽ በርክጥ ርቱዕ (ትክክለኛ) አስተምህሮ ነውን?

---

[7] Hailu Yohannes, Birth Right #1-#4 http://www.hailu.hyfm.org/Videos16.htm

[8] ዝኒ ከማሁ።

[9] ግለሰቡ ይህን ምላሽ የሰጡት፣ "እምነት ሪያሊትን መካድ ነውን?"፣ "አሞኝ አላመመኝም ማለት ግብዝነት አይደለምን?" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ነው። ግለሰቡ "ፋክት" እና "ሪያሊቲ" የሚሉት ቃላት ምን ሐሳብ እንደ ወከሉ ማብራሪያ አልሰጡም። ነገር ግን አንድ አስገራሚ ነገር በዚህ ንግግር ውስጥ ማስተዋል ይቻላል። ይኸውም ግለሰቡ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ትምህርት ሁሉ ሪያሊቲ ነው"። ካሉ በኋላ፣ "ኢየሱስ ሪያሊቲውን ክዷል" ብለዋል። ምን ማለታቸው ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ሪያሊቲ ከሆነ፣ ኢየሱስ እንዴት መጽሐፍ ቅዱስን ይክዳል? ኋላ "እውነት ምንድን ነው?" በሚለው ርእስ ጉዳይ ላይ አጭር ዳሰሳ እናደርጋለን። ከዚህ ትንታኔ የምንግረው ነገር ሪያሊትን መካድ "እምነት" ለሚለው ቃል የሚቀርብለት ትርጓሜ ሳይሆን፣ "ውሸት" የሚለውን ቃል የሚወክለው ፅንሰ ሐሳብ ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ እንደ ግለሰቡ ትምህርት፣ "እምነት" ማለት "ሐሰትን መናገር" ማለት ነው። በርግጥ ኢየሱስ አልሞተችም ያለው እውነታውን ለመካድ ነውን? በቅዱሳት መጻሕፍት ሞት በእንቅልፍ የተመሰለበት ምክንያት "ሪያሊቲውን ለመካድ" ተብሎ ነውን? "ኢየሱስ ያስነሣው የሞተውን ሰው ሳይሆን ያንቀላፋውን ሰው ነው" የሚለው ንግግራቸው ጥሬ ውሸት አይደለምን?

# እምነት በፍልስፍና አስተምህሮ ውስጥ

እምነት ስለሚባለው ስለዚህ ወሳኝ ቃል፣ ብሉያትና ሐዲሳት የሚሰጡት ትርጓሜና ትንታኔ ምንድን ነው? ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ከሌላው የትምህርት ዘርፍ በተለይ ደግሞ በሥነ ዕውቀት ውስጥ ከሚቀርበው ትንተና ጋር ግጣሙ ምንድን ነው? በሌላ አነጋገር የነገረ መለኮቱ ትንተና ከፍልስፍናውና ከሳይንሱ ፅንሰ ሐሳብ የተለየ ነውን?

ሰው ሁሉ እምነት አለው። ለሃይማኖቱ የተሰየፈውን ሰማዕት ጨምሮ፣ በህልዎተ እግዚአብሔር አላምንም እስከሚለው ግራጫ ከሐዲ ደረስ፣ በእምነት ውሎ ያድራል። ለዚህም ነው እምነት የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የፍልስፍናና የሳይንስ ጭብጥ ነው የሚባለው። ሱባኤ ለገቡ መነኮሳት ብቻ ሳይሆን፣ ጉባኤ ለተቀመጡም ሊቃውንት ትልቅ የውይይት ጀንዳ ነው። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ፣ እምነት የሃይማኖተኞች ግብር ብቻ ሳይሆን፣ የኢአማንያንም የህልውና ማዕከል ነው።

ይህ ምን ያህል ትክክል ነው የሚለውን ጉዳይ በአጭሩ ላስረዳ። የፍልስፍና ዘርፍ በሆነው በሥነ ዕወቀት ትምህርት (epistemology)፣ አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ ዕውቀት አለው የሚባለው፣ ግለሰቡ ያውቀዋል የተባለው ጉዳይ:— (1) እውነት ሲሆን፣ (2) ነገሩን ሲያምነው እንዲሁም (3) ማረጋገጫ ሲያቀርብለት ነው[10]። ይህ በፍልስፍናው ዓለም፣ "ሥሉሳዊ የዕውቀት ነባቤ ቃል" ("tripartite theory of knowledge") በመባል ይታወቃል። የታጨቀ ሐሳብ ስለሆነ እንዳፍታታው ይፈቀድልኝ።

በቅድሚያ የእውነትን መስፈርት እንመልከት። ዕውቀትን ገንዘብ ለማድረግ እውነት ወሳኝ ጉዳይ ነው። እውነት ባልዋለበት ሜዳ ዕውቀት በፍጹም ሊገኝ አይችልም። አንድ ሰው፣ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የተገደሉት በ1969 ዓ.ም ነው" ቢል፣ ኋላ ግን በ1966 ዓ.ም እንደ ተገደሉ ከታሪክ መዛግብት ቢረዳ፣ ግለሰቡ ንጉሡ ቀድሞ የተገደሉበትን ዘመን ***ያውቅ*** ነበር ማለት ይቻልም። የማያውቅ ከሆነ ደግሞ፣ ዕውቀት አለው ሊባል አይችልም። ይህ ዕውቀት እውነትን ማዕከል እንደሚያደርግ የሚያስገነዝብ ነው። አንድ ሰው፣ "ጨረቃ የተፈጠረችው ከአይብ ነው" የሚለውን ሐሰብ ለማስረዳት ትልቅ ጥራዝ ያለው መጽሐፍ ቢጽፍ፣ ይህን ድርሳን እንደ ዕውቀት መድብል ልንመለከተው አንችልም። የመጽሐፉ ግዙፍነት እውነተኝነቱን ሳይሆን፣ ዘብዛባነቱን የሚያሳይ ነውና። ምክንያቱም ጨረቃ ከአይብ ስላልተሠራችም። ከዚህ የምንማረው ቊም ነገር እውነት የዕውቀት ማዕከል መሆኑን ነው።

የዕውቀት ሌላው መስፈርት ደግሞ ***እምነት*** ነው። ዕውቀት እውነትን ብቻ ሳይሆን እምነትንም የግድ ይፈልጋል። አንድ ሰው 5+3=7 መሆኑን ዐውቆ ነገር ግን ባያምነው ዕወቀት አለው ልንለው አንችልም። ይህ ሰው "አምስት ከሦስት ጋር ሲደመር ውጤቱ ስንት ነው" የሚለው ጥያቄ ቀርቦለት "7 መሆኑን ስለማላምን 5 ነው" ቢል፣ ወይም ከ7 የተለየ ማናቸውንም ዐይነት መልሶች ቢሰጥ፣ ግለሰቡ ስሌቱን ያውቀዋል ማለት አይቻልም። አንድ ሰው "በማቀዝቀዣው ውስጥ ወተት እንዳለ ዐውቃለሁ፤ ነገር ወተት መኖሩን አላምንም" ቢል በአነጋገሩ መደነቃችን አይቀርም። "መኪና ሰውን ድጦ እንደሚጐዳ ወይም እንደሚገድል ዐውቃለሁ፣ ነገር ግን ይህን በጭራሽ አላምንም" ቢለን፣ የሐኪም ርዳታ የሚያስፈልገው ወፈፌ አርገን ነው የምንቈጥረው። ሰው የሚያውቀውን ነገር ያምነዋልና፤ ካላመነው አለወቀውም ማለት ነው። የዕውቀት ሌላው መስፈርት እምነት ነው የሚባለው ለዚህ ነው።

---

[10] እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር እስከ 1963 ዓ.ም ድረስ ዕውቀት ማለት ***የተረጋገጠ፣ እውነታኛ እምነት*** ነው የሚለውን አስተምህሮ የተገዳደረ አንዳችም ምሁር የለም። በ1963 ዓ.ም ላይ ኤድመንድ ጊደር (Edmund L. Gettier) የተባለ አሜሪካዊ ፈላስፋ ሦስት ገጽ ባለው መጣጥፍ፣ ከዘመነ አፍላጦን ጀምሮ እስከ በ1963 ዓ.ም ደርስ ይሠራበት የነበረውን ንድፈ ሐሳብ ክፉኛ ተገዳድሯል። ይህ የጊደር ጽሑፍ ዕውቀት እነዚህን ሦስት መሠረታውያን ነጥቦች ብቻ ነው ወይስ ሌላም ተጨማሪ ግብኣት ይፈልጋል፣ የሚለውን ጉዳይ ለክርክር ያቀረበ እንጂ፣ እነዚህ ሦስት መሠረታውያን ግባቶች አያስፈልጉም እንዳላለ ልብ ይሏል።

*የዕውቀት ሦስተኛው መስፈርት **ማስረጃ** ነው፡፡ ዕውቀት እውነትንና እምነትን ብቻ ሳይሆን፣ ማስረጃንም ይፈልጋል፡፡ ማስረጃ ያልታከለበት ዕውቀት፣ ግምት እንጂ ዕውቀት አይደለም፡፡ ቊም ነገሩን እንዲያዋዛልኝ አንድ ምሳሌ ልጠቀም፡፡ በ1500 ሩጫ ከገለቴ ቡርቃ ይልቅ፣ ገንዘቤ ዲባባ ክብረ ወሰን ትሰብራለች የሚል አቋም ብይዝ፣ ይህን አቋም የያዝሁት ግን በገንዘቤ ዲባባ መልከ ቀናነት ተማርኬ ቢሆን፡፡ እንደ ተናገርሁት የማታ ማታ ገንዘቤ ክብረ ወሰን ብትሰብር፣ "ተስፋዬ ስለዘገንዘቤ የክብረ ወሰን ማሻሻል የሰጠው አስተየየት፣ ዕውቀትን ማዕከል ያደረገ ነው" ማለት አይቻልም፡፡ ትክክለኝነቴ በአቦ ሰጥ የተገኘ እንጂ፣ ዕውቀትን የተደገፈ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የልጅቱ ቊንጅና ከሩጫ ችሎታዋ ጋር በተለይም ክብረ ወሰን ከመስበሯ ጋር በአገርም ሆነ በዘመድ አይገናኝም፡፡ ስለዚህ የግምቴ ትክክልኝነት በአጋጣሚ የሆነ እንጂ፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ስለዚህ የነገሩ ዕውነት መሆን ዕድል እንጂ ዕወቀት አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ ዕውቀት ማስረጃን እንደሚፈልግ ያስተምራል፡፡*

*ከዚህ አጭር ትንታኔ የምንማረው ቊም ነገር፣ ዕወቀት ሦስት መሠረታውያን አዕማዶች ላይ የተመሠረተ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም **እውነት፣ እምነትና ማስረጃ** ናቸው፡፡ ለዚህ ነው እነዚህን የዕውቀት ግብኣቶች፣ "ሥሉሳዊ የዕውቀት ነባቤ ቃል"* ("tripartite theory of knowledge") *በመባል ይጠራናቸው፡፡ ይህ እንግዲህ በፍልስፍናው ዓለም በስፋት የቀባይነት ያለው የሥነ ዕውቀት ትንታኔ መሆኑን ልብ ይሏል*[11]፡፡

*ይህ ደግሞ እምነት የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የዕውቀት ዘርፍ ለሆኑ ለየትኛውም የትምህርት ዘርፎች፣ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ በእምነት የምንኖረው እኛ ሰማያውያኑ ብቻ ሳንሆን፣ ምድራውያኑም ጭምር ናቸው፡፡ በእምነት የማይኖሩት ደመ ነፍሳውያኑ እንስሳትና ቀልቡን የሳተ ወፈፌ ብቻ ነው፡፡ በአጠቃላይ ያለ እምነት አንዳችም ንድፈ ሐሳብ፣ አንዳችም ዕውቀት፣ አንዳችም እውነት በአጠቃላይ አንዳችም ሕይወት የለም፡፡ ዕውቀት ያለ እውነት፣ እምነትና ማስረጃ መቆም እንዳማይችለው ሁሉ እምነትም ያለመረጃና ያለእውነት በፍጹም እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በሊቃውንቱ ጉራ፣ "የሰው ልጅ ሁሉ አማኒ ነው" የሚባለው በዚህ ምክንያት ይመስለኛል፡፡*

*"እውነት ምንድን ነው?" የሚለው ጭብጥ፣ ኋላ ለውይይታችን እጅግ ስለሚጠቅመን "በነካ እጃችን" የእውነትንም ትንታኔ በአጭሩ ተመልክተን እንለፍ፡፡*

## *እንግዲያው እውነት ምንድን ነው?*

*እውነት፣ እምነትና ማስረጃ የዕውቀት ወሳኝ ግብኣቶች እንደ ሆኑ ተመልክተናል፡፡ አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ ዕውቀት አለኝ የሚለው፣ እነዚህ ሦስት መሠረታውያን ንጥረ ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ አልያ ግን ግለሰቡ ዕውቀት አለኝ ስላለ፣ ዕውቀት አለው ማለት አይቻልም፡፡ እንግዲያው እውነት ራሱ ምንድን ነው?*

*እውነት ምንድን ነው ለሚለው ጉዳይ ሦስት መሠረታውያን ነባቤ ቃላት (አመለካከቶች) አሉ፡፡ **አንደኛው፣** ዝምደታዊ/ጉድኝታዊ የእውነት ንድፍ ሐሳብ* (Correspondence Theory of Truth) *የሚባለው ነው፡፡ እንደ ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ፣ አንድ ነገር እውነት ነው ሊባል የሚችለው ዐረፍተ ነገሩ ከገሐዱ ዓለም* (reality) *ጋር ጥምረት ወይም ጉደኝት ፈጥሮ* (correspond) *ሲገኝ ነው፡፡ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ መብራራት ያለባቸው ቊልፍ ወይም ሐሳቦች አሉ፤ ይኸውም፡—*

---

[11] *አሜሪካዊው ፈላስፋ* Edmund Gettier *እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር* 1963 *ዓ.ም ያቀረበው አጭር ጽሑፍ ይህን ነባር ዶክትሪን በተወሰነ ደረጃ ጥያቄም ቢሆን ጥያቄ ላይ መጣሉን መግለጽ እወዳለሁ፡፡ በምን መልክ የሚለው ጉዳይ ግን፣ የሌላ ጽሑፍ ጭብጥ ነው፡፡*

## 1) እውነት ተሸካሚ (Truth-bearer)

እውነት ተሸካሚ የሚባለው የእውነት ፋይዳው (truth value) እውነት አልያም ሐሰት የሆነ ዐረፍተ ነገር ብቻ ነው[12]፡፡ "ሁለትና ሁለት ድምሩ አራት ነው" ወይም "ሣር አረንጓዴ ተክል ነው" የሚሉ ዐረፍተ ነገሮች እውነት ተሸካሚ ይባላሉ፡፡

## 2) እውነት ፈጣሪ (Truth-maker)

እውነት ፈጣሪ የምንለው እውነት ተሸካሚውን እውነት እንዲሆን ያደረገው ነገር ማለት ነው፡፡ "ሣር አረንጓዴ ተክል ነው" የሚለው ዐረፍተ ነገር እውነት ሊሆን የሚችለው በገሐዱ ዓለም (reality) ሣር አረንጓዴ ቀለም ይዞ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ አንድ ሰው ሣር አረንጓዴ ቀለም እንዳለው ማወቁም ሆነ ያለማወቁ የእውነት ፋይዳውን ቅንጣት ታህል አይቀይረውም (ለምሳሌ ግለሰቡ ዐይነ ስውር ወይም ቀለም አይለዩ መሆኑ ዐረፍተ ነገሩ እውነት አይደለም እንድንል አያደርገንም)፡፡

## 3) ጉድኝታዊ መስተጋብር (Correspondence relation)

በእውነት ተሸካሚውና በእውነታው ፈጣሪው መካከል ያለው ግንኙነት ጉድኝታዊ መስተጋብር ይባላል፡፡ አንድ ነገር ከሌላው ነገር ይበልጣል ወይም ያንሳል ለማለት፣ ማነጻጸሪያ ወይም ማገናዘቢያ ያስፈልጋል፡፡ በምን መስፈርት አነጻጽረነው ነው ይበልጣል ያንሳል፣ ረጅም ነው ቀጭን ነው ወዘተ የምንለው የሚለው ጉዳይ ወሳኝ ነው፡፡

በዚህ መልክ ስንመለከተው ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ፣ እውነት ተሸካሚውን ከእውነት ፈጣሪው ጋር የሚያነጻጽር ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡




"እኔ የአሸናፊ የሥጋ ወንድም ነኝ" ብል፣ ይህ ንግግሬ እውነት ሊሆን የሚችለው አሸናፊ የተባለው ግለሰብ፣ ከእኔ እናት ወይም ከእኔ አባት (ወይም ከሁለቱም) መወለድ ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እውነት ተሸካሚ የሆነው ዐረፍተ ነገር እውነት ፈጣሪ ከሆነው ከገሐዱ ዓለም ጋር ተነጻጽሮ መሳ ለመሳ ሆኖ ሲገኝ (ትክክለኛ ጉድኝት ሲፈጥር) እውነት ነው ይባላል፡፡

**ሁለተኛው፣ ቅንብራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ** (The Coherence Theory of Truth) በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሐሳብ መሠረት አንድ ነገር እውነት ነው የሚባለው እውነት ተሸካሚው ከገሐዱ ዓለም ጋር ጥምረት መፍጠሩ ሳይሆን፣ በግለሰቡ መረጃ ድር ውስጥ አንዱ መረጃ ከሌላው መረጃ ጋር መቀናበሩ ነው፡፡ በዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ውስጥ ያለን ሰው ከራሱ ውጪ በሆነ መረጃ የሚያምነውን ትክክለኛነትና ስሕተት ማስረዳት አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ እውነትን ኅሊናዊ ስለሚያደርገው፣ ማንም የእኔ እውነት ነው፣ የአንተ ደግሞ ሐሰት ነው ማለት አይችልም፡፡

**ሦስተኛው፣ ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ** (Pragmatic Theory of Truth) የሚባለው ነው፡፡ እንደዚህ ንድፈ ሐሳብ ደግሞ አንድ ነገር እውነት ነው የሚባለው ጉዳዩ ጠቃሚ ሆኖ ወይም አዋጪ

---

[12] አስተያየት፣ ጥያቄ፣ አመለካከት፣ ፍላጎት ወዘተ የእውነት ፋይዳቸው እውነት ወይም ሐሰት መሆን ስለማይችሉ በሥነ በፍልስፍናው ዓለም ዐረፍተ ነገር አይባሉም፡፡

ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው[13]። ከታች ያየናቸው ሁለቱ ንድፈ ሐሳቦች (ቅንብራዊ እንዲሁም ገቢራዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ) ለአንጻራዊነት መቀፍቀፍ ትልቅ ሚና ተጫውቶአል። ምክንያቱም ለአንድ ሰው ጠቃሚ ወይም አዋጪ የሆነው ነገር ለሌላው ሰው እንደዚያ ላይሆን ይችላልና። ይህ ደግሞ እውነትን ነባራዊ መሠረት ነች የሚለውን ይጻረራል።

እኔ እስከማውቀው ድረስ ሁሉም ክርስቲያኖች ጉድኝታዊ መስተጋብርን ይቀበላሉ። በአንጻሩ ከዚህ ውጪ ያሉትንም ማናቸውንም የእውነት ንደፈ ሐሳቦች ይቃወማሉ። አንድ ሰው ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብን ክዶ፣ "ክርስቶስ ወደ አብ የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ነው፤ ማንኛውም ሰው ድነትን ለማግኘት ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሊያመን የገባዋል" እንዴት ማለት እንደሚችል አይገባኝም።

እስካሁን የተነጋገርንበትን ሐሳብ ሰብሰብ እናድርገው። ዕወቀት ሦስት መሠረታውያን አዕማዶች ላይ የተመሠረተ ነው። እነርሱም ***እውነት፣ እምነትና ማስረጃ*** ናቸው። ዕውቀት ያለ እውነት፣ እምነትና ማስረጃ መቆም እንዳማይችለው ሁሉ እምነትም ያለመረጃና እውነት በፍጹም እውን ሊሆን አይችልም። እውነት ማለት ደግሞ እንደ ገሐዱ ዓለም የሆነ ነገር ወይም አነጋገር ወይም ዐዋጅ ማለት ነው።

## እምነት በቅዱሳት መጻሕፍትና በደርዛዊ ነገረ መለኮት

በቅድሚያ እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ምን ዐይነት ሐሳብ እንደሚወክል እንመልከት። በመቀጠል ነገረ መለኮታውያን፣ አንኳር አንኳር የሚባሉትን መረጃዎች በማሰባጠር እምነት የሚለውን ቃል እንዴት እንደ ተነተኑት እንመለከታለን።

የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ የእምነትን ማንነትና ጠባይ የተነተኑልን በቀጥታ ሳይሆን በምሳሌ ነው። ይህን ገለጻ ተከትለን ስንሄድ ስለእምነት ዐራት ዐበይት ፅንሰ ሐሳቦችን እናገኛለን።

***አንደኛው እምነት አለመናወጥን፣ አለመበገርን፣ አለመፈታትን ያመለክታል።*** በዚህ አገባቡ በአምላክ ጫንቃ ላይ ተደላድሎ መቀመጥን (ኢሳ. 60÷4)፣ እንደ ችንካር መተከልን (ኢሳ. 22÷23)፣ ጽኑ ስፍራ መያዝንና (1ሳሙ 2÷35፤ 1ነገ. 11÷38)፣ ታምኖ መጽናትን (ኢሳ. 7÷9) ይገልጻል። በብሉይ ኪዳን ቃሉ የእግዚአብሔርን ጽኑነት ይኸውም እንደ ቃሉ የሚገኝ አምላክ መሆኑን ለመግለጽ የገባበት ጊዜም አለ (ኢሳ. 49÷7፤ ኤር 42÷5)። በዘዳግም 7÷9 ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን፦ "አምላክህ እግዚአብሔር…የታመነ አምላክ እንደ ሆነ ዕወቅ"። ይህ እግዚአብሔር አባያ (ዋሾ) እንዳልሆነ፣ ይልቁንም በነገር ሁሉ እሙን መሆኑን የሚያስረዳ ነው። እርሱ የተናገረውን ቃል አጥፎ ወይም የገባውን ኪዳን ሽሮ አያውቅም። በተናገረው ቃል ታምኖ፣ በገባውም ኪዳን ጸንቶ የሚኖር ጌታ ነው። በአንጻሩም በእርሱ የታመኑትን፣ ሁለንተናቸውን በእርሱ ላይ የጣሉትን፣ ወደ እርሱም የሸሹትን አሳፍሮ አያውቅም (መዝ. 31÷5-6)።

***ሁለተኛው እምነት ፍጹም መታመንን የሚያመለክት ነው።*** ሰው ሊታመን የሚገባው ጽኑ፣ ጥብቅ እንዲሁም ዘላላማዊ በሆነ ነገር ነው። ድጥ በሆነ፣ አንሸራቶ በሚፈጠፍጥ ለመታመን የሚሞክር ማንም ሰው የለም። እግዚአብሔር ታሪክ አለው፤ ዝናም አለው። ይህም ታሪኩ አይለወጤነቱ ነው። እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፣ "እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ስለዚህ የጠፋችሁ አይደላችሁም" (ሚልክያስ 3÷6)። ርዳታም ሆነ ምሕረት ፈልገው ወደ እርሱ የሚመጡትን ሜዳ ላይ ጥሎ አያውቅም (መዝሙር 92÷2)። አብርሃም በእግዚአብሔር ያመነው (ዘፍጥረት 15÷6) ዘሮቹም በእግዚአብሔር እንዲያምኑ

[13] A belief P is true if and only if P works or is useful to have.

(ዘፀአት 4÷5-31) የታዘዙት፣ መታመን የሚችል አምላክ በመኖሩ ነው። እግዚአብሔርም ታማኝነቱን በየተለያዩ ጊዜዎች አሳይቶአል።

**ሦስተኛው እምነት እውነተኛነትን የሚያመለክት ፅንሰ ሐሳብ ነው።** በእግዚአብሔር የምንታመነው፣ አንዳች ሳንሠጋ በእርሱ ላይ የምንቆመው፣ በእርሱ ላይ የምንደገፈው እውነተኛ ስለ ሆነ ነው። እሙን በመሆኑም የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ ምንም ሳንጠራጠር እንቀበላለን። ምክንያቱም እርሱ የታመነ ነው። ንጉሥ ዳዊት በጸሎቱ እንዲህ ብሎ እንደ መሰከረው፣ "ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ! አሁንም አንተ አምላክ ነህ፤ ቃልህም እውነት ነው" (2ሳሙኤል 7÷28)። ዳዊት በመዝሙሩ የእግዚአብሔርን እውነተኛነት የሚነግረን፣ "የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው፤ ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ" በማለት ነው (መዝሙር 89÷14-15)። መዝሙረኛው በብዙ ምንባባት የእግዚአብሔርን እሙንነት ከእውነተኛነቱ ጋር አያይዞ እናገኛለን (መዝሙር 119÷43:142:151:160)።

**አራተኛው እምነት በክርስቶስ ወጀአዊ ሥራ ማመንን የሚገልጽ ነው።** በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እምነት ሁሉ ጊዜ የታይዞ የሚገኘው ከድነት ጋር ነው። በመስቀሉና በትንሣኤው የሚያምኑ ሁሉ ድነት ያገኛሉ (1ቆሮንቶስ 15÷3-4:11)። በሌላ በኩል ደግሞ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታና የመንፈስ ፍሬ ተደርጎ የቀረበበትም ጊዜ አለ (ኤፌሶን 2÷8-9፤ገላትያ 5÷22)። እንደ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ትምህርት ሰዎች የሚጸድቁት በእምነት ነው (ሮሜ 5÷1)። በሌላ አነጋገር፣ "ሰው የሚጸድቀው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ የሙሴን ሕግ በመፈጸም እንዳልሆነ እናውቃለን፡ እኛም ሕግን በመፈጸም ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን እንድንጸድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነናል" (ገላትያ 2÷16)። ስለዚህ ሥጋ ለባሽ ሁሉ መመካት የሚያስፈልገው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። እምነት "ከእኔ የሆነ አንዳች ነገር የለም ይልቁንም ሁሉ የሆነው በአንተ ነው" የምልበት ቋንቋ ነው።

በአጠቃላይ በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ እምነት ትልቅ የነገረ መለኮት እሳቤ ነው። እምነት ማለት በራስ መታመንን ማቆብ ብቻ ሳይሆን፣ በራስ መታመንን መካድ ጭምር ነው። እምነት ማለት ራስን ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር እጅ ላይ መጣል ማለት ነው። እምነት ማለት እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት የገባልንን ቃል ታግሦ መጠበቅ ማለት ነው። እምነት በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም መታመንና እርሱን ፍጹም መታዘዝ ነው።

ከላይ ካየናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች በመነሣት፣ የደርዛዊ ነገረ መለኮት ምሁራን የእምነትን ፅንሰ ሐሳብ በሚከተለው መልክ ተንትነውታል። ምናልባት እነዚህን ***የእምነት ሥሉሳዊ ባሕርያት*** ልንላቸው እንችላለን። እነርሱም እምነት እንደ ***ዕውቀት፣*** እምነት እንደ ***ትምክህት*** እንዲሁም እምነት እንደ ***ስሙሙነት*** ናቸው[14]። ነባብያነ መለኮት ለእነዚህ የእምነት ባሕርያት ሙያዊ ቃላት ቀምረዋል፤ ይህም ስያሜ ከላቲን የተወሰደ ነው። እምነት እንደ ዕውቀት "ኖቲሺያ" (notitia)፣ እምነት እንደ ትምክህት "ፊዱሺያ" (fiducia) እንዲሁም እምነት እንደ ስሙሙነት "አሰንሰስ" (assensus) ናቸው።

**እምነት እንደ ዕውቀት ("ኖቲሺያ" notitia)** የሚለውን ሐሳብ በቅድሚያ እንመልከት። ለእምነት ዕውቀት ወሳኝ ነገር ነው። ዕውቀት ሲባል ደግሞ መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች እንዲሁም የክርስትናን ንጽርአተ ዓለም ማወቅ የግድ ይላል፣ "ወዳጆች ሆይ፤ አብረን ስለምንካፈለው ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጉቼ ነበር። ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ ለመምከር እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" (ይሁዳ 3)።

**እምነት እንደ ትምክህት ("ፊዱሺያ" fiducia)** ሲባል፣ በነገሩ እውነተኛነት ላይ ያለንን ርግጠኝነት ብቻ ሳይሆን፣ በምናምነውም አካል ላይ ያለንን ትምክህት የሚያሳይ ነው። ይህም ፈቃድን ሙሉ

---

[14] Faith as knowledge *(notitia),* faith as assent *(assensus)* and faith as commitment *(fiducia).*

ለሙሉ የሚሻ ጉዳይ ነው። ክርስትና በአስተምህሮ የተገደበ ትምህርት ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መታመንም ይጨምራል፣ "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል" (ዮሐንስ 10÷27)።

**እምነት እንደ ስሙሙነት** ("አሰንሰስ"assensus) ሲባል፣ ምን ማለት እንደ ሆነ አጭር ማብራሪያ መስጠት ያስፋልጋል። አለማመን፣ ጥርጣሬና እምነት ማጣት የተለያዩ ነገሮች ናቸው[15]። አለማመን የነገሩን እውነተኝነት ተረድቶ ነገር ግን ሐቁን ያለመቀበል አለማመን ይባላል። ጥርጣሬ ግን አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ሥነ ልቡናዊ በሆነ መልኩ፣ በጥርጣሬ ውስጥ መኖር ነው። እምነት ማጣት ደግሞ፣ ማመን እፈልጋለሁ ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ማመን አልቻልሁም፤ ስለዚህ ርዳታ እፈልጋለሁ ማለት ነው።

ጥርጣሬ ሁሉ ከዕውቀት ማነስ የሚመነጭ አይደለም። ስሜታዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳዮች ጣልቃ ገብተውበት እምነት ሊታወክ ይችላል። ለምሳሌ ጥሩ የአባት ፍቅር ያላገኘ ልጅ፣ "እግዚአብሔር አባታችን ነው" የሚለው ንግግር እንብዛም ላይገባው ይችላል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ልናነሣው የሚገባን አንድ መሠረታዊ እውነት አለ። አንድ ሰው እምነት አለው ሲባል፣ እምነቱ መቶ በመቶ ነው ማለት አይደለም ወይም ጥርጣሬ አድሮበታል ሲባልም እምነቱ ዜሮ ከመቶ ነው ማለት አይደለም። አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ያለው እምነት በመጠን ደረጃ ይለያያል። አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖች በአንድ ጉዳይ ላይ ያላቸውን ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ሲያነሡ፣ አንዳችም እምነት እንደሌላቸው አድርገው ይገምታሉ። ይህ ስሕተት ነው፤ ስለዚህ እምነት በመጠን ደረጃ እንደሚለያይ ሊጠፋን አይገባም (በዚህ ቦታ "all or nothing" የሚባለው አስተሳሰብ አንዳችም ቦታ የለውም)። ስለዚህ እምነት ስሙሙነት ነው ሲባል፣ መቶ በመቶን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አይደለም።

## ማጠቃለያ

እምነት ምንድን ነው የሚለውን ጉዳይ በትክክል ለመረዳት እነዚህ ሦስት መሠረታውያን ነጥቦች (የእምነት ሥሉሳውያን መሠረቶች) በትክክል መረዳት ይስፈልጋል። በአጭሩ ኖቲሽያ በክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ላይ መሠረታዊ ዕውቀት መያዝ ሲሆን፣ አሰንሰስ ደግሞ ከክርስትና እውነት ጋር መስማማት ነው። ፌዱሺያ ደግሞ ከእውነታው ጋር የተስማማ ሕይወት መኖር ናቸው።

# የእምነት እንቅስቃሴ ስለእምነት፣ ያለው አስተምህሮ

እንቅስቃሴው ስለ "እምነት" ያለውን አግድም ዐደግ ትምህርት በትክክል በመረዳት ስሕተቱን በትክክል ማከም የሚቻለው፣ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ኩታ ገጠም የሆኑትን ነጠቦች ማለትም "በአዎንታዊ ዐዋጅ" እንዲሁም "በጸሎት" ላይ የሚሰጡትን ትምህርቶች በትክክል መገንዘብ ሲቻል ነው። ስለዚህ በቅድሚያ፣ የእንቅስቃሴው አንጋፋ መምህራን በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሚሰጡትን ትንታኔ፣ ከራሳቸው ጽሑፎች በቀጥታ በመጥቀስ ከተመለከትን በኋላ፣ ወደ ሒሱ እንዘልቃለን።

## እምነት

እንቅስቃሴው፣ "በእምነትህ ላይ እምነት ይኑርህ" ይለናል። እንደ መምህራኑ ትንታኔ፣ አምላክ ራሱ እምነት አለው (ማር 11÷22)። ይህ አምላክ ገንዘቡ አድርጎታል የሚባለው ዐይነት እምነት ክርስቲያኖችም ይኖራቸው ዘንድ፣ አምላክ ራሱ በስጦታ መልክ ለአማንያኑ ማኅበረሰብ አከፋፍሏል

[15] Unbelief, doubt, and lack of belief.

(ሮሜ 12÷3፤ ኤፌ 2÷8)፡፡ ይህ እምነት ደግሞ፣ ተራራን የማናወጥ ኀይል አለው፡፡ አምላክ ራሱ ዓለማትን የፈጠረው፣ ይህን ዐይነቱን እምነት እንደ ግብዐት በመጠቀም ነው (ዕብ 11÷3፤ እንዲሁም ሮሜ 4÷17)[16]፡፡

እንዲያውም የእንቅስቃሴው መምህራን፣ እምነት ብቻ ሳይሆን፣ ከአንደበታችን የሚወጡ ንግግሮች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ኀይል ስላላቸው፣ ክርስቲያን የሆነም ሆነ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው፣ የሚናገረው ንግግር እውን እንደሚሆን አምኖ (እርግጠኛ ሆኖ) ከተናገረ፣ ንግግሩ ግዝፍ (ሥጋ) በመንሣት ወደ እውነታነት (ገሓድነት) ይቀየራል፡፡ ምክንያቱም ይህ (ማመን እንዲሁም ያመኑትን ነገር መናገር) በአማኒውም ሆነ አማኒ ባልሆነው ሰው ውስጥ በጕልሕ የሚሠራ፣ የማይነቀስ የማይገሠሥ ቀመር ነው[17]፡፡ ለዚህ የሚጠቀሰው ጥቅስ ኢየሱስ፣ "***ማንም*** ያለው ነገር እንዲደረግለት ***ቢያምን***" (ማቴ 11÷23) ይሆንለታል ብሏል የሚለው ነው[18]፡፡

የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህር የሆኑት ኬኔት ሐጊን ይህን ጒዳይ በተመለከተ እንዲህ ይላሉ፡—

> "ያልዳኑ ሰዎች ሲሳካላቸው የማየቴ ጒደይ ግራ ይገባኛል፡፡ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኔ ሰዎች [ይህ ዐይነቱን] ውጤት አያዩም፡፡ ጎጥኣን ምን እያደረጉ ነው ለሚለው ያገኘሁት መልስ፣ ከዚህ ዐይነቱ የእግዚአብሔር ሕግ ጋር መተባበራቸው ነው፤ ይኸውም የእምነት ሕግ ነው፡፡"[19]

በአጠቃላይ፣ "ማናቸውንም ነገር ከእግዚአብሔር ማግኘት የሚፈልግ ሰው፣ በእምነቱ ላይ እምነት ሊኖረው ይገባል"[20]፡፡ እንግዲያው እምነት ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጥያቄ የእንቅስቃሴው መሪዎች፣ "ኀይል ነው"[21] የሚል ትርጒም ይሰጡታል፡፡ ይህ ደግሞ እምነት ያልሆነውን ነገር እውን እንዲሆን፣ ያልተፈጠረውን ነገር መፍጠር እንዲችል አድርጎታል (ሮሜ 4÷17)[22]፡፡ እምነት ረቂቅ ነገር ቢሆንም፣ የማይታየውን ነገር እንዲታይ የማድረግ ከፍተኛ ኀይል አለው[23]፡፡

የእንቅስቃሴው መምህራን፣ "እውነተኛ እምነት ቁሳዊ የሆነውን እውነታ አይቀበለም" ባዮች ናቸው (ሮሜ 4÷19፣ 2ቆሮ 4÷18፣ 5÷17)[24]፡፡ ስለዚህም እምነት ምክንዮአዊና ምክንያታዊ ሳይሆን፣ ከአምክንዮ ሕግጋት ጋር የሚጻረር ነገር ግን እንዲያው በጭፍን የሚታመን ነገር ነው[25]፡፡

የእንቅስቃሴው መምህራን እስካሁን ከተመለከትነውም በተጨማሪ ስለ እምነት ሌላም ገለጻ አላቸው፡፡ ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ እምነት የሚለውን ቃል የሚጠቀመው በዐላፊ ጊዜ ነው (ዕብ 11÷1)፤ ነገር ግን ተስፋ በትንቢታዊ (በመጻኢ) ጊዜ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡፡ ስለዚህ እምነት አሁን

---

[16] Hagin, *New Thresholds of Faith* ገጽ 74-76፡፡ Copeland, *The haws of Prosperity,* ገጽ 18-19፡፡

[17] Charles Capps, *The Tongue: A Creative Force* (Tulsa: Harrison House 1976), ገጽ 132፡፡

[18] Hagin, *Having Faith in Your Faith* (Tulsa Keneth Hagin ministries, 1980) ገጽ 3-5፡፡ በዚህ ክፍል "ማንም" የሚለው ቅጽል፣ አማኒውን ማኅበረሰብ እንጂ፣ የማያምነውን ሰው እንደ ማይጨምር ከክፍሉ ዐውድ ያስተውሏል፡፡ ፡፡

[19] Hagin, *Haring Faith in Your Faith,* ገጽ 3-4፡፡ ሕጉ በማንኛውም ሰው ላይ እውን የሚሆን ሕግ ነው ከተባለ፣ በቤተ ክርስቲያናቸው ስዎች ሕይወት ውስጥ ለምን ሳይሠራ ቀረ የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ አግባብነት አለው፡፡

[20] ዝኒ ከማሁ ገጽ 5፡፡

[21] Copeland, *The Force of faith* በተለይ ገጽ 13-14:19 እንዲሁም Capps, *Faith and Confession,* ገጽ 44፡፡

[22] Hagin, *New Thresholds of Faith,* ገጽ 7-8 እንዲሁም Right and Wrong Thinking Copeland, Our Covenant with God, ገጽ 38-39፡፡

[23] Hagin, *Real Faith,* ገጽ 26፡፡ *Knowing What Belongs to Us* ገጽ 6-7:10:29፡፡ Price, *How Faith Works,* ገጽ 25፡፡

[24] Price, *How Faith Works,* ገጽ 31፡፡

[25] Hagin, *Words,* ገጽ 32፡፡

በእጃችን ያለ ነገር እንጂ (ማር 11÷23)፣ ወደ ፊት በእጃችን የሚገባ ጉዳይ አይደለም[26]። ስለዚህ፣ ተስፋ የምታደርገውን ነገር ትተህ፣ ያለህን እምነት በመጠቀም የምትፈልገውን ነገር አሁን በእጅህ አስገባ"[27] ይሉናል።

## አዎንታዊ ዐዋጅ

እንደ እንቅስቃሴው መምህራን ትንታኔ፣ ማንኛውንም ነገር እንደምናገኝ ብናምንና ያመነውን ነገር እንዳገኘነው ብናውጅ ያሻነውን (የፈለግነውን) ነገር በእጃችን እናስገባለን (ሮሜ 10÷10)። ይህ የከጀልነውን (ያሻነውን) ነገር የምናገኝበት "ቀመር" ወይም "ሕግ" ነው[28]። የምናገኛቸው ክፉም ሆኑ ደግ ነገሮች፣ በእምነት ሆነን በቃላት በምንገልጻቸው ንግግሮች ይወሰናሉ[29]። እንቅስቃሴው ይህን ባዕድ ሐሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለማስደገፍ ሙከራ የሚያደርገው በሚከተሉት ሁለት መንገዶች ነው:— ***አንደኛው፤*** አምላክ ዓለማትን ለመፍጠር እንደ ግብዐት (መሣሪያ) አድርጎ የተጠቀመው ቃላትን ነው (ዘፍ 1፤ መዝ 33÷6:9፤ ዕብ 11÷3)። ይህም ቃላት በጽንፈ ዓለም (በሁለንታ/በአጽናፈ ዓለም) ውስጥ እጅግ ኀይለኛ ነገር መሆኑን የሚያመለክት ነው።[30] ***ሁለተኛ፤*** በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት፣ ሰዎች በሚናገሩት ነገር ዕጣ ፈንታቸው እንደሚወሰን ይገልጻሉ። ይኸውም የምንናገራቸው ማናቸውም ነገሮች፣ የሕይወትም ሆነ የሞት ኀይል አላቸው (ምሳሌ 18÷21)። መጽሐፍ ቅዱስ ለምትናገሩት ነገር ጥንቃቄ ይኑራችሁ የሚለው፣ ቃላት ክፉም ሆነ ደግ ነገር የማድረግ ኀይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ ነው (ምሳሌ 6÷2፤ ማቴ 12÷37)[31]። "እምነት" እና "ዐዋጅን" በተመለከተ አንድ የእንቅስቃሴው መምህር የሰጡት ገለጻ እስካሁን የተመለከትነውን ነገር በጥሩ ምንገድ ይሰበስበዋል:— "እምነት ፈጣሪ ኀይል ነው። ቃል ደግሞ ይህን ፈጣሪ ኀይል የሚሸከም መሣሪያ ነው። እምነት እግዚአብሔርን ለሥራ የሚቀሰቅሰው ሲሆን፣ ፍርሓት ደግሞ ሰይጣንን ለሥራ ያነሣሣዋል"[32]። "አንዲት ጠንቋይ እንዲህ እንዲህ የሚል ነገር ነገራኛለች:— 'በጥንቈላ አዕዋፍን እንዲሁም ሰዎችን በቃል እንዴት እንደምንገድል ተምረናል። ሊሸነፉ የሚችሉበትን የተወሰኑ ቃላት በመናገር፣ በአዕዋፋትም ሆነ በሰዎች ላይ በሽታን እንዴት ማምጣት እንደምንችል ተምረናል። ቃል በመናገር አዕዋፋትን እገድላለሁ!' አለችኝ እኔም፣ 'እግዚአብሔር ሆይ ሰይጣን ይህ ዐይነቱ ኀይል እንዳለው አለውቅም ነበር' አልሁት። እግዚአብሔርም፣ 'ሰይጣን በቃል ይገድላል፤ አንተ ደግሞ በቃል ሕይወትን መስጠት ትችላለህ' አለኝ። እኛ ክርስቲያኖች በአፋችን ላይ ያለውን የቃል ኀይል በውል አናውቀውም[33]። ስለዚህ፣ 'ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርባችሁ ጌታ ሆይ ፈቃድህ ቢሆን' የሚል፣ እምነትን የሚገድል ጸሎት በፍጹም! በፍጹም! አትጸልዩ። ትሕትና ይመስላችሁ ይሆናል፤ ነገር ግን ጅልነት ነው። ይህን ማለታችሁ እግዚአብሔርን ሞኝ ነህ እንደ ማለታችሁ ነው። ይህ ዐይነቱ ጸሎት እምነታችሁን ከመሠረቱ በመንቀል፣ ፍርሓት በሕይወታችን

---

[26] Copeland, *The Force of Faith,* ገጽ 9-12። Price, *How Faith Works,* ገጽ 48።

[27] Hagin, *The Real Faith* ገጽ 41-42። Capps, *Faith and Confession* ገጽ 15።

[28] Hagin *The Real Faith* ገጽ 25።

[29] Hagin, *New Thresholds of Faith* ገጽ 43። Price, *How Fath Works,* ገጽ 111።

[30] Hagin, *New Thresholds of Fath* ገጽ 10።

[31] ዝኒ ከማሁ ገጽ 77። Capps, *The Tongue,* ገጽ 12-14። Price, *How Faith Works* ገጽ 58።

[32] D.R Mcconnell ገጽ 146 ከ Benny Him, "Double Portion Anointing Part #3" audiotape#A 031791-3 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[33] ዝኒ ከማሁ 146 ከBenny Hinn, *"Praise the Lord"* Program on TBN (1June 1989) ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

እንዲነግሥ በማድረግ ሰይጣን እንዲሠራ ያደርገዋል"[34]። አሁን ደግሞ የመጨረሻውን ነጥብ ማለትም እንቅስቃሴው ስለ ጸሎት ያለውን ትምህርት በአጭሩ እንመልከት።

## ጸሎት

እንደ እንቅስቃሴው መምህራን አስተምህሮ፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠንን ነገር ስጠን ብሎ መጸለይ እንዲሁም፣ ቀድሞ ያደረገውን ነገር አድርግ ብሎ መማጸን ስሕተት ነው። እግዚአብሔር ቀድሞውንም ቢሆን በክርስቶስ ወጀአዊ ሥራ ድነትን፣ የኀጢአት ይቅርታን፣ ፈውስን እንዲሁም ብልጥግናን ሰጥቶናል[35]። ስለዚህ ቀድሞ የሰጠውን ነገር ስጠን እንዲሁም ቀድሞ ያደረገውን ነገር አድርግ ብሎ መጸለይ፣ የሰንካላ እምነት ዐይነተኛ ምልክት ነው። ስለዚህ፣ "ፈቃድህ ቢሆን" ብሎ መጸለይ ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም ድነት፣ ፈውስ፣ የኀጢአት ይቅርታ እንዲሁም ብልጥግና ቀድሞውኑም ቢሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ናቸውና። ስለዚህ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከመጸለያችን በፊት፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው የቱ ነው የሚለውን ጥያቄ ከቃለ እግዚአብሔር አንጻር መመለስ ያስፈልጋል። ይህን ካረጋገጥን በኋላ፣ እነዚህ ነገሮች የእኛ መሆናቸውን በእምነት ሆነን በቃላት ይፋ ማድረግ ማለትም ማወጅ ነው። ስለዚህ በጸሎታችን ልንከውነው የሚገባን ነገር፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያከብር "ማዘዝ" ብቻ ነው (ዮሐ 14÷13-14 እንዲሁም 15÷7 ባሉት ክፍሎች "ጠይቁ" የሚለው ቃል ይህ ዐይነቱን ትርጒም ወክሎ እናገኘዋለን)[36]። ይንን ካረጋገጥን በኋላ፣ እነዚህ ነገሮች የእኛ መሆናቸውን በእምነት ሆነን በቃላት ይፋ ማረግ ማለትም ማወጅ ነው። ስለዚህ በጸሎታችን ልንከውነው የሚገባን ነገር፣ እግዚአብሔር ቃሉ እንዲያከብር ማዘዝ ብቻ ነው። የእንቅስቃሴው ሌላ መምህር ይህን ጒዳይ በሚከተለው መልክ ያብራሩታል:—

> "አማኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ በኢየሱስ ስም የማዘዝ መብቱ አላችሁ። ቃሉን መሠረት እስካደረጋችሁ ድረስ፣ ቃሉን እውን እንዲያደርግ የማዘዝ መብት አላችሁ። ምክንያቱም መሠረት ያደረጋችሁት ቃሉን ነውና። ታማኝ የሆነ ሰው ቃሉን እስኪሰጣችሁ ድረስ በቃሉ የታሰረ ነው"[37]።

## የእምነት እንቅስቃሴ ስለእምነት የሚያስተምረው ትምህርት ግምገማ

የእንቅስቃሴው አንጋፋ መምህራን በሦስት መሠረታውያን ነጥቦች ላይ ስለእምነት ያላቸውን አስተምህሮ በቅኝት መልክ ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል ይህ ትምህርት ምን ያህል ትክክል ነው የሚለውን ጒዳይ፣ በቃለ እግዚአብሔር ወደመመርመሩ እንዘልቃለን።

የብሉይም ሆነ የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ እግዚአብሔር እምነት አለው የሚለውን ትምህርት በጭራሽ አያስተምሩንም። ምክንያቱም እምነት ማለት በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ነገር ወይም ደግሞ በተለየ አካል መተማመን ወይም መመካት ማለት ነውና። "እግዚአብሔር እምነት አለው" የሚለውን ዐረፍተ ነገር መጠቀም የምንችለው፣ እግዚአብሔር በራሱ ኀይልና ጥበብ የተማመናል እንዲሁም የሚያውቃቸው ነገሮች እሙን መሆናቸውን ያምናል በሚለው ትርጒሙ ወይም ዐውድ ብቻ ነው። ነገር ግን የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን እግዚአብሔንም ሆነ ሰዎችን አስመልክተው እምነት

---

[34] ዝኒ ከማሁ።

[35] Hagin, *You Can Write Your Own Ticket with God,* ገጽ 18። Capps *Faith and Confession* ገጽ 15።

[36] Hagin, *Name of Jesus,* ገጽ 73-74።

[37] Copeland, *Our Covenant With God,* ገጽ 40-41።

የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት፣ አንድ ሰው የሚያምነውን ወይም የሚፈልገውን ነገር በአንደበቱ በመናገር የሚያገኝበት ወይም እውን ያልሆነውን ነገር እውን የሚያደርግበት፣ ዘላለማዊ ከሆነው መንፈሳዊ ሕግጋት ጋር ተጣምሮ የሚሄድ ኀይል አድርገው ነው፡፡ ይህ ዐይነቱ ትምህርት አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የሌላው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከብሉያትም ሆነ ከሐዲሳት ትምህርት ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው፡፡

ክርስቲያኖች ሁሉ የሚያድን እምነት እንደ ተሰጣቸው እሙን ነው፤ ነገር ግን ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ተኣምር የመሠራት እምነት የለውም፡፡ በርግጥም እምነት የአምላክ ችሮታ (ስጦታ) ነው፡፡ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራንም በዚህ እውነት ይስማማሉ (ሮሜ 12÷3፤ ኤፌ ኤፌ 2÷8)፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር፣ "ተራራን የሚያናውጥ" እምነት ለሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ አልሰጠም፡፡ ጳውሎስ እንደሚለው ይህ ዐይነቱ እምነት ከመንፈሳዊ ስጦታዎች መኻል አንዱ ነው (1ቆሮ 12÷9፤ 13÷2፤ ሮሜ 12÷3:6)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ዐይነት ስጦታ የላቸውም የሚለው ከዚህ የተነሣ ነው (ሮሜ 12÷4-6፤ 1ቆሮ 12÷4-6: 14-19:28-30)፡፡ ጌታችን፣ "ተራራን ስለሚነቅለው" እምነት ሲያስተምር (ማቴማቴ 21÷21፤ ማር 11÷23)፣ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ የዚህ ዐይነቱ እምነት ባለቤት ነው አላለም፡፡ ይህ አይነቱ እምነት ስጦታ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፣ "እንደ ፈቀደ" የሚሰጠው (1ቆሮ 12÷11)፡፡ አንዳንዴ እግዚአብሔ ለማመን አስቸጋሪ የሆነውን ነገር እንድናምን እምነት ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፣ ይህ ዐይነቱ እምነት ክርስቲያኖች ሁሉ፣ ሁሉ ጊዜ ገንዘባቸው ያደረጉት ጉዳይ ነው አይልም፡፡

ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች እምነት አላቸው ስንል፣ በተጨባጭ የተረዱትን ነገር መቀበላቸውን በሚገልጽ ትርጉም ብቻ መሆን አለበት (ሥነ ዕወቅት በሚባለው የፍልስፍና ጥናት ውስጥ ዕውቀት፣ እምነትን፣ እውነትንና ማስረጃን ይፈልጋል የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው)፡፡ ክርስቲያናዊው እምነት ሰዎች ሁሉ ያላቸው ነገር ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አምላክ ሰዎች ለድነታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ጌትነት ላይ እንዲታመኑ፣ የሚሰጣቸው ሰማያዊ ስጦታ ነው፡፡

## የእምነት ግምገማ

ቃለ እግዚአብሔር እምነት፣ "ኀይል ነው" አይልም፡፡ ሰዎች እምነትን እንደ መሣሪያ በመጠቀም እውን ያልሆነውን ነገር እውን የሚያደርጉበት ወይም መንፈሳዊውን ቁሳዊ የሚያደርጉበት ወይም ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያስገድዱበት መሣሪያ ነው የሚለው ትምህርት ፍጹም ስሕተት ነው፡፡ መምህራኑ ይህን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለማስደገፍ የሚጠቀሙባቸውን ሁለት የሐዲስ ኪዳን ምንባባትን እንመልከት፡፡ አምላክ ቃልን በማወጅ፣ እውን ያልሆነን ነገር መፍጠር ይችላል የሚለው ጥቅስ የሚጠቀሰው፣ "ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ" የሚለው የሮሜ 4÷17 ክፍል ነው፡፡ ነገር ግን የሌለውን ነገር እውን ማድረግ የሚችለው አብርሃም ሳይሆን፣ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ አብርሃም በእግዚአብሔር ያመነበት ዐይነተኛው ምክንያት፣ "ለሙታን ሕይወት ስለሚሰጥ፤ ያልነበረውንም እንደ ነበር ስለሚያደርግ ነው" (ቍ 17)፡፡ የተስፋውን ቃል የሰጠው እንዲሁም የተስፋውን ቃል የፈጸመው ራሱ እግዚአብሔር ነው (4÷20-21)፡፡

"ክርስቲያን ጤንነትንና ብልጽግናን የራሱ እንደ ሆኑ በማመን፣ ያመነውንም ነገር እውን ይሆንለት ዘንድ በማወጅ፣ ያሻውን ነገር ያገኛል" ለሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት የሚጠቀሰው ጥቅስ ኤፌሶን 1÷3 ነው፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በክፍሉ ላይ የሚዘረዝራቸው በረከቶች ሁሉ ቁሳዊ ሳይሆኑ መንፋሳውያን ናቸው:—

1. የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን (ቍ 5)
2. በደሙ የተደረገውን ቤዛነታችንንና የኀጢአት ስርየት ማግኘታችን (ቍ 7)

3.የፈቃዱን ምስጢር ማወቃችን (ቍ 9)
4.የእግዚአብሔር ርስት ወራሽ መሆናችን (ቍ 11)
5.በመንፈስ ቅዱስ መታተማችን (ቍ 13)

በዐውዱ ውስጥ የምናገኛቸው እነዚህ በረከቶች ሁሉ መንፋሳውያን እንጂ፣ ስለአካላዊ ጤንነት ወይም በንዋይ/በገንዘብ በኵል ስለሆነው ብልጥግና የሚናገሩ አይደሉም። ወይም መንፈሳዊው ነገር በእምነት ቁሳዊ መሆን እንደሚችል የሚናገሩ አይደሉም።

እምነት በጭራሽ ቁሳዊ የሆነውን እውነታ የሚክድ አይደለም። ለምሳሌ የአብርሃምን ታሪክ ከሮሜ ምዕራፍ 4 እንመልከት። በክፍሉ አብርሃም የአካሉን ማርጀት እንዲሁም ልጅ ለመውለድ ዐቅም እንደ ሌለው ሲክድ አንመለከትም። ምውት የሆነውን የእርሱንና የባለቤቱን አካል፣ ራሱ እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ ሕያው በማድረግ ልጅ እንሚሰጣቸው አመነ እንጂ። ይህ የእምነት ሰው፣ ሙት የሆነውን የእርሱንና የባለቤቱን አካል እየካደ ሲናገር አንመለከትም (ቍ 19)። እንቅስቃሴው ግን እምነት እውነታን መካድ ነው እንዳለ ልብ ይሏል።

የእንቅስቃሴው መምህራን፣ "የሚታየውን እንጂ የማይታየውን ባንመለከት" (2ቆሮ 4÷18) የሚለውንም ጥቅስ አዘወትረው ይጠቅሳሉ። ነገር ግን በክፍሉ ሐዋርያው ጳውሎስ እያለ ያለው፣ ቁሳዊ እውነታዎችን እንካድ ሳይሆን፣ የሕይወታችን መሠረት ሊሆን የሚገባው የሚታየውን ጊዜያዊ የሆነው ነገር ሳይሆን፣ ዘላለማዊና ከሚታየው ነገር በላይ የሆነው ነገር መሆን ይገባዋል የሚል ትምህርት ነው። እንዲያውም ሐዋርያው በዚሁ ዐውድ፣ "የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ" የሚለው ሐረግ የሚያሳየን፣ አካላችን እንደሚሞትና እንደሚበሰብስ የሚያስረግጥ ነው። የእንቅስቃሴው መምህራን ግን ይህ ዐይነቱን የጳውሎስ ንግግር፣ "አሉታዊ ዐዋጅ" በማለት ያጣጥሉታል። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ቁሳዊ እውነታን መናገር ነውር ነው ወይም እውነታን መካድ እምነት ነው የሚል ትምህርት አያስተምርም።

"በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና" (2ቆሮ 5÷7) የሚለው የጳውሎስ ንግግር፣ "ማየትን" ወይም የገሐዱን ዓለም እውነታ የሚቃወም አይደለም። ነገር ግን ሕይወት የሚመዘነው አሁን እየኖርንበት ባለው ሕይወት ስላልሆነ፣ በእግዚአብሔር ዘላላማዊ ተስፋ ካመን፣ ያለመሞትና በትንሣኤ ጊዜ የከበረ ሕይወት ባለቤቶች እንሆናለን ለማለት ነው (ቍ 1-8)።

ልብ ልንላው የሚገባን ሌላው ነጥብ፣ እምነት ምክንያታዊነትን (አመክንዮን) ይቃወማል የሚለው አስተሳሰብ ስሕተት ነው። እምነት በፍጹም ኢመክንያታዊነት አይደለም። እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንተና፣ እምነት ዓለማትን የፈጠረውና ዓለማትን በእውነት በሚያስተዳድረው ልዑል አምላክ መተማመን ስለሆነ። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት የዕውቀትና የመረዳት መጠናችንን ውሱንነት ያገናዘበ ነው። "በራስህም ማስተዋል አትደገፍ" (ምሳሌ 3÷5) ማለት፣ ኢምክንያታዊ ሁን ማለት ሳይሆን፣ ሕይወትህን ለመምራት በራስህ ብቃት ስለሌለህ በእግዚአብሔር ዕውቀትና እርሱን በማክበር ኑር ማለት ነው (ቍ 6-7)።

እምነት የአሁን ጊዜ (Present tense) ጕዳይ ነው፣ የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች ላይ፣ የአሁን ጊዜ የሚያመለክቱ ግሦስና (is) ቃላት (now) ጥቅም ላይ የዋሉት፣ ለሐሳብ ፍሰትና የዐረፍተ ነገሩን ሽግግር ለማሳለጥ እንጂ፣ የጊዜን ቅደም ተከተል እንዲያመለክቱ ታስቦ አይደለም፤ ለምሳሌ:— 1ቆሮ 7÷1 ይመለከቷል። የአሁን ጊዜን የሚየመለክተው ረዳት ግሥ (is) የእምነት ትንታኔ ለመግለጽ የገባ እንጂ፣ ጊዜን ለማመልከት አይደለም።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ እምነት የዐላፊ፣ የአሁን እንዲሁም የመጪውን ጊዜ እውነታ አቀናጅቶ የያዘ ነው። አምነት የአሁን ጊዜ እውነታ ስለሆነ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት

የሚያሳይ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር እንደሚወደን፣ ከእኛ ጋር እንደሚኖር ወዘተ (ሮሜ 5÷13)፡፡ እውነት የዐላፊ ጊዜ እውነታንም ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ ኢየሱስ እኛን ለማዳን የሚተውና ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው ባለፉት ዓመታት ስለሆነ (ሮሜ 10÷9፤ 1ቆሮ 15÷1-11)፡፡ እምነት የሚጪውንም ጊዜ እውነት ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ ይኸውም በሕይወት ዘመናችን እውን ያልሆኑ ነገሮች፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ይፈጽምልናል የምንላቸው ቃል ኪዳኖች (ተስፋዎች) ሁሉ መጪውን ጊዜ የሚያመለክቱ ናቸው (ዕብ 11÷6)፡፡ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳንም የምንማረው ይህን ባሕርይ ነው (ሮሜ 6÷8፤2ጢሞ 1÷12)፡፡ ይህ የሚያሳየን እምነት መጪውንም ጊዜ የሚያመለክት እንደ ሆነ ነው (1ተሰ 4÷14)፡፡

እምነት እግዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ እውን ያደርገዋል (ይፈጽመዋል) ብለን የምንታመንበት መሠረት እንጂ፣ አንድ ነገር የእኛ እንዲሆን የምናስገድድበት (የምናዝበት) መሣሪያ አይደለም፡፡ እምነት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን መግቦት (Providence) ዛሬም ሆነ ወደ ፊት የምናረጋግጥበት ምልዕቅ ነው፡፡

## የአዎንታዊ ዐዋጅ ግምገማ

የእንቅስቃሴው መምህራን፣ አዎንታዊ ዐዋጅን አስመልክቶ አበክረው ከሚጠቅሷቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት መኻል ሮሜ 10÷10 ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ይመስለኛል፣ "ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፤ በአፉም መስክሮ ይድናልና"፡፡ የእንቅስቃሴው መሪዎች ከዚህ ጥቅስ በመነሣት የተፈለገን ነገር ማግኘት የሚቻልበትን "ቀመር" ቀምረዋል፤ "ሕግ" ደንግገዋል፡፡ ነገር ግን የክፍሉ ዐውድ ይህን በጭራሽ የሚደግፍ አይደለም፡፡ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን፣ የሮማውያን ቄሳሮች አምላክ ነን የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ ግዛተ ዐፄአቸውንም አምላከ ገዝ (ቴዎክራቲክ) ብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ቄሳር ጌታ ነው ማለትም የሮማውነት ዐይነተኛ ምልክት ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ግን ቄሳር በፍጹም ጌታ አይደለም፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው በሚለው አቋማቸው ጸኑ፡፡ በዚህ ምክንያት ለአናብስትና ለአናምርት ይሰጡ እንደ ነበር፣ በግንድ ላይ ታስረው በእሳት ይቃጠሉ እንደ ነበር ታሪክ ያስተምረናል፡፡ በዚያን ዘመን ኢየሱስ ጌታ ነው ብሎ በአፍ መመስከር፣ የሕይወት ዋጋ የሚያስከፍል ትልቅ ወንጀል ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር…ትድናለህ" ብሎ ሲናገር፣ ይህን ታሳቢ ባደረገ መልክ ነው፡፡ ስለዚህ ሰው የኢየሱስን ጌትነት በልቡ አምኖ፣ "ቄሳር ጌታ ነው" ብሎ በአፉ ሊመሰክር አይችልም፡፡ ምክንያቱም አምላካችን እግዚአብሔር፣ "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ" ብሏልና፡፡

ዕብራውያን ደግሞ የብሉይ ኪዳንን ሕግ በመፈጸም ጽድቅ እንደሚገኝ ያምናሉ፤ በአፋቸውም ይመሰክራሉ፤ ነገር ግን ዕብራውያኑ ይህን በማድረጋቸው ትክክል አይደሉም (ሮሜ 9÷30፤ 10÷3)፡፡ ማመንና መመስከር ብቻውን ለውጥ አያመጣም፡፡ ከዐውዱ እንደምንመለከተው ጳውሎስ እመኑ፤ በአፋችሁም መስክሩ የሚለው፣ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ፤ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው" ነው፡፡ ይህን ታሪካዊ ንግግር በማዛባት የሰዎች ንግግር አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት አለው የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት በዚህ ጥቅስ ላይ መደገፍ በፍጹም አይችልም፡፡ ሌላው፣ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ፤ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው" እኛ ብናምን ወይም ባናምን፤ በአፋችን ብንመሰክር ወይም ባንመሰክር፣ እውነታውን እውነት ከመሆን የሚቀንሰው (የሚከለክለው) አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ኬኔት ሐጊንም ሆኑ ቢጤዎቻቸው፣ "አንድ ሰው ድኛለሁ ብሎ ካላወጀ በስተቀር፣ ድነት አያገኝም"[38] እንዲሁም ሰው የተናገረውን ማናቸውም ነገሮች ያገኛል የሚለው ትምህርታቸው፣ በቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ አይደለም፡፡

---

[38] Hagin, *Understanding Our Confession* ገጽ 4፡፡

ከላይ እንደ ተመለከትነው፣ የምናገኛቸው ክፉም ሆኑ መልካም ነገሮች ሁሉ፣ በእምነት ተሞልተን በቃላት በምንገልጸው ነገር ይወሰናሉ" ለሚለው ትምህርት የእንቅስቃሴው መምህራን የሚጠቅሱት ሌላው ጥቅስ ማቴዎስ 9፥29፣ "እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዐይኖቻቸውን ዳሰሰ" የሚለውን ነው። ነገር ግን ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ወደ እርሱ ሲመጡ፣ ፈውስ ገንዘባቸው እንደ ሆነ እንዲያምኑ፣ ተፈውሻለሁ ብለው እንዲያውጁ" ሲያበረታታቸው ወይም "እኔ የምፈውሳችሁ እምነት ሲኖራችሁ *ብቻ* ነው" ሲላቸው አንመለከትም። ይልቁንም፣ ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን?" (ቍ 28) ብሎ ሲጠይቃቸው እንጂ፤ ይህ የሚያሳየን ዐይነ ስውሮቹ፣ የተፈወሱት በእምነታቸው ሳይሆን፣ በኢየሱስ ፈዋሽነትና ደግነት ነው። ኢየሱስ ሊፈውሳቸው እንደሚችል ማመናቸውን ተጠየቁ እንጂ፣ "ፈውስ የእኛ ነው" ብለው እንዲያውጁ አልተጠየቁም። ፈውስን ከኢየሱስ ለመቀበል እምነት አስፈላጊ ነው፤ ነገሬ ግን ለፈውስ ብቸኛው ምክንያት አይደለም።

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን አሉታዊ ዐዋጅ የሚሉትን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ የሚጠቀሙባቸው ጥቅሶች፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ያለውን ኀይል ለመግለጽ፣ የሚጠቀምባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ቃል ኀይለኛ የሆነበት ምክንያት የእግዚአብሔር ስለሆነ (እግዚአብሔር ስለተናገረው) እንዲሁም እውነት ስለሆነ እንጂ (ሮሜ 4፥16-21)፣ ቃላት በራሳቸው ኀይል ስላላቸው አይደለም። ዘማሪው፣ "እርሱ ተናግሮአልና ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፤ ጸኑም" (መዝ 33፥9) ያለበት ምክንያት፣ "ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲፈራው፤ በዓለም የሚኖሩም ሁሉ ከእርሱ የተነሣ እንዲደነግጡ" (ቍ 10-11) ነው። እንግዲህ ፍሬ ነገሩ እዚህ ላይ ነው:— እግዚአብሔር ያለው ወይም የተናገረው ለዘላለም ጽንቶ ይኖራል፤ ሰዎች ያሉት ግን (በነሲብና በግምት) ሊፈጸምም ላይፈጸምም ይችላል። ዘማሪው፣ "ሰብአውያን የሚናገሩት ቃል እውን እንዲሆን፣ በእምነት ተሞልተው ይናገሩ" የሚል ምክር አይመክርም። ይልቁንም ዘማሪው እስራኤል አምላኳ የሆነውን እግዚአብሔርን እንድትፈራ፣ ምሕረቱንም ተስፋ እንድታደርግና ርዳታውንም እንድትሻ ይመክራል (ቍ 16-22)።

የቃለ እግዚአብሔርን ሥልጣን ኀይል በማተማ ከሚታወቁ ክፍሎች መኻል ኢሳይያስ 55፥11 አንዱ ነው፣ "ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል፤ የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም"። እግዚአብሔር እንዲህ ያለበት ምክንያት እስራኤል የተሐድሶ ዘመኗ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት ፊቷን ወደ አምላኳ እንድትመልስ ለመግለጽ ነው (ቍ 6-13)። ይህ የሚሆንበት ምክንያት፣ እግዚአብሔ ፍጹም ስለሆነ፣ መንገዱ ከሰብአውያን መንገድ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ የራቀ ስለሆነ፣ እርሱ የሚለው ሁሉ እውነት እንደ ሆነ እርግጠኞች ነን (ቍ. 8-9) ።

መጽሐፈ ምሳሌ ቃላት መንፈሳዊ ኀይል አላቸው የሚል ትምህርት አያስተምርም። እንዲያውም በርካታ የመጽሐፈ ምሳሌ ክፍሎች፣ የሰብአውያን ቃላት በራሳቸው ኀይል እንደ ሌላቸው ያስተምራሉ (እባክዎን እነዚህን ክፍሎች በጥሙና ያንብቧቸው ምሳሌ 14፥23፤ 17፥10፤ 26፥23:26፤ 29፥19)።

የእንቅስቃሴው መምህራን፣ የምንናገራቸው ማናቸውም ነገሮች የሕይወትም ሆነ የሞት ኀይል አላቸው፣ ለሚለው ትምህርታቸው የሚጠቅሱት ሌላው ጥቅስ፣ "በአፍህ ቃል ተጠመድህ፤ በአፍህ ቃል ተያዝህ" (ምሳ 6፥2) የሚለውን ነው። ነገር ግን ክፍሉ የሚያወራው፣ ለጐረቤቶቹ ዋስ ሆኖ፣ በዋሱ መሠረት ስለተያዘ ሰው ነው፣ "ልጄ ሆይ ለጐረቤትህ ዋስ ብትሆን፣ ስለሌላ ሰው እጅህን አጋና ብትመታ፣ በአፍህ ቃል ተጠመድህ፤ በአፍህ ቃል ተያዝህ" (ምሳ 6፥1-2)። ቃላት የሕይወትና የሞት ኀይል አላቸው ለሚለው ትምህርት የሚጠቀስ ሌላው ጥቅስ፣ "ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው፤ የሚወድዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ" (ምሳሌ 18፥21) የሚለው ክፍል ነው። ቃላት የሕይወትና የሞት ኀይል አላቸው የተባለው፣ ቃላት የእምነትን ኀይል ስለሚያስተላልፉ ሳይሆን፣ የምንናገራቸው ንግግሮች

ጥሩም ሆነ መጥፎ ውጤት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነው። በዚህ ዐውድ የሰነፍ ንግግር ጠብን ስለሚጭር በዚህም የሰዎችን ሕይወት ስለሚቀጥፍ ነው (ቍ 6-7)። ጕራጌ ዘመዶቻችን፣ "በለፈለፉ በአፍ ይጠፉ" እንደሚሉት መሆኑ ነው።

ለአዎንታዊ ዐዋጅ የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ ማቴዎስ 12÷36-37 ነው። በክፍሉ ኢየሱስ ፈሪሳውያን በንዝላልነት የሚናገሩትን ከንቱ ንግግር ሲነቅፍ ይታያል። የእንቅስቃሴው መሪዎች ከዚህ ጥቅስ በመነሣት አሉታዊ ዐዋጅ የሚያስከትለውን ጥፋት የሚገልጽ ቀመር ቀምረዋል፣ ይኸውም፣ "ለምትመኘው ነገር ጠንቃቃ ሁን፤ ምክንያቱም የተመኘኸውን ነገር ድንገት ከተናገርኸው ታገኘዋልህና"። ነገር ግን በዚህ ክፍል ኢየሱስ ለማስተማር የፈለገው ነገር ፍጹም ከዚህ የተለየ ነው። ይኸውም ኢየሱስ ሲያወግዘው የነበረው ንግግር ፈሪሳውያን መንፈስ ቅዱስን (እግዚአብሔርን) የመሳደባቸውን ጕዳይ ነው (ቍ 31-32)። መንፈስ ቅዱስንም የመሳደባቸው ውጤት፣ በራሱ በእግዚአብሔር እንደሚፈረድባቸው ወይም እንደሚቀጡ እንጂ፣ አሉታዊ ነገር በመናገራቸው ምክንያት ብቻ፣ የተናገሩት ንግግር በራሱ አሉታዊ ውጤት ያመጣባቸዋል ማለት አይደለም። ለምንናገራቸው አዎንታዊም ሆኑ አሉታዊ ንግግሮች ተጠያቂዎች መሆናቸውን እሙን ነው፤ የምንጠየቀውም የተናገርነውን ነገር የምናምንና የተናገርነውም ነገር እውን እንዲሆን ጠንክረን የምንሠራ ከሆነ ብቻ ነው።

እንደ እንቅስቃሴው መምህራን ትምህርት ከሆነ፣ "ጕስቋላና ምስኪንም ድኻም ዕውርም የተራቈትህም መሆንህን ስለማታውቅ" (ራእይ 3÷17) የሚለው የጌታ ንግግር የሰይጣን ውሸት ነው ማለት ነው? በፍጹም አይደለም። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያንማ፣ "ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ፤ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል" ነበረች፤ ነገር ግን ይህን ማለቷ ያለችውን እንድትሆን አላደረጋትም። እንዲያውም እውነቱ ከተናገረችው ነገር ተቃራኒ ሆኖ ስለተገኘ ነው ራሱ ጌታ ጕስቋላ ነሽ፣ ምስኪን ነሽ፣ ድኻ ነሽ፣ ዕውር ነሽ እንዲሁም የተራቈትሽ ነሽ የሚላት።

## የጸሎት ግምገማ

እግዚአብሔር የሰጠንን ነገር ስጠን ብሎ መጸለይ እንደማያስፈልግ፣ እንደ እንቅስቃሴው መምህራን ሁሉ እኛም እናምናለን። እግዚአብሔር ኀጢአታችንን እንዲዋጀን ልጁን ልኮልን ሳለ እንደ ገና ላክልን ብለን መጸለይ አያስፈልገንም፤ እንዲህ ዐይነቱ ጸሎት ስሕተት ነው (ሮሜ 9÷15-18፤ ያዕ 4÷6-10)። የእንቅስቃሴው መምህራን፣ በዮሐንስ 14÷3-14 እንዲሁም 15÷7 "ጠይቁ" የሚለው ቃል፣ "ፈልጉ" የሚል ትርጕም አለው ማለታቸው ስሕተት ነው። በአማርኛቹም ሆነ ተኣማኒነት ባላቸው የእንግሊዝኛ ቅጆች ላይ "ኤቴዎ" የሚለው የግሪክ ቃል የተተረጐመው፣ "ፈልጉ" ተብሎ ሳይሆን፣ "ጠይቁ" ተብሎ ነው። ቃሉ የሚገኝበትን ሌላ ዐውድ ስንመለከት፣ እውነቱ ይኸው ሆኖ ነው የምናገኘው (ሉቃስ 23÷23፤ 23÷52፤ 7÷7-11)። ኧረ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያከብር "እዘዙት" ይላልን? በርግጥስ ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ከልዑል አምላክ ለምኖ ማግኘት ከሚፈልግ የሰው ልጅ የሚጠበቅ መንፈስ/አተያይ ነውን?

እንደ እንቅስቃሴው አስተምህሮ፣ "ፈቃድህ ቢሆን" ብሎ መጸለይ ስሕተት ነው። ይህ ትምህርት ጕልሕ የሆኑ ሁለት መሠረታውያን ችግሮች አሉበት። አንደኛው ቃለ እግዚአብሔር፣ "ፈቃድህ ቢሆን" ብለን መጸለይ እንዳለብን ያበረታታል። ጌታ ስለ ጸሎት ባስተማረው ስፍራ (ማቴ 6÷10)፣ "ፈቃድህ ይሁን" ብለን መጸለይ እንደሚገባን ገልጾልናል። ጌታ ራሱ በዚህ መልክ ይጸልይ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (ማቴ 6÷39)። ያዕቆብም፣ "ብንኖር ጌታም ቢፈቅድ በሉ" ሲል ያመክረናል (ያዕ 4÷15)። ሐዋርያው ዮሐንስም፣ "በእርሱ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል" (1ዮሐ 5÷14) ይላል። የሐዋርያው ጳውሎስም ጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማዕከል

ያደረገ ነበር (ለምሳሌ ሮሜ 1 ይመለከቷል)። ሁለተኛው ቃለ እግዚአብሔር ከበሽታችን ሁሉ እንደምንድን ወይም የገንዘብ ችግር ሲያልፍ እንኳ አንደማይነካን ያስተምረናልን? በማርቆስ 11÷24 ኢየሱስ፣ "የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፤ ይሆንላችሁማል" ሲል፣ እምነት የምናምነውንና የምንናገራቸውን ማናቸውንም ነገሮች እውን የሚያደርግ ኀይል ነው ማለቱ ነው? በፍጹም አይደለም። በክፍሉ ትምህርት መሠረት ነገሮችን እውን የሚያደርገው፣ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እኛ አይደለንም።

ቃለ እግዚአብሔር፣ "በእኔ ብትኖሩ፣ ቃሎቼም ብእናንተ ቢኖሩ፣ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል" (ዮሐንስ 15÷7) ይለናል። "የምንወደው ነገር ሁሉ" ሊሆንልን የሚችለው፣ እኛ በጌታ ስንኖርና ቃሎቹም በእኛ ሲኖሩ ነው፤ ይኸውም፦

1. ክፉ ባልሆነ ልብ (ምኞት) ጸሎታችንን ማቅረብ (ያዕ 4÷3)፣
2. ከሰዎች ጋር ያልንን ግንኙነት ማስተካከል፣ (1ጴጥሮስ 3÷7)፣
3. እንደ ፈቃዱ መጸለይ (1ዮሐ 5÷14)።

ይህን አሟልተን፣ "የምንወደውን ነገር ሁሉ" እንዲሰጠን መጸለይ እንችላለን፤ ነገር ግን የሚሆንልን፣ ልዑል እግዚአብሔር፣ "ይረባቸዋል ስለዚህም ይሁንላቸው" ብሎ የሚፈቅድልን ነገር ብቻ ነው፤ ያውም በራሱ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት። ምክንያቱም የሚያስፈልገንን ነገርም ሆነ፣ መቼ በትክክል እንደሚጠቀመን እርሱ ያውቃልና። እኛ እግዚአብሔርን ልናስገድደው የምንችል ትናንሽ አማልክት ሳንሆን፣ ***በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ብእርሱ ላይ የምንደገፍ፣ ጸሎታችን ያልተሰማ በመሰለን ጊዜ እንኳ በእርሱ የምንታመን የእግዚብሔር የጸጋ ልጆቹ ነን።***

## ማጠቃለያ

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን እምነት፣ አዎንታዊ ዐዋጅና ጸሎትን በተመለከተ ያላቸው ትምህርት፣ በግማሽ እውነት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። ነገር ግን ተዳባልቆ የቀረበው ገሚሱ ውሸት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሳይሆን፣ እጅግ ሲበዛ ገዳይ እንዲሁም የማታ ማታ ብዙዎችን መና ያስቀረ ትምህርት ነው። በእግዚአብሔር የምንታመን ከሆነ፣ እግዚአብሔር አስደናቂ ነገር እንደሚያደርግ እሙን ነው፤ ነገር ግን እኛ በእርሱ በመታመናችን እግዚአብሔር ተገዶ ተኣምራትን ያደርጋል የሚለው ትምህርት ስሕተት ከመሆኑም ባሻገር ነውረኛ አስተሳሰብ ነው።

አዎንታዊ በሆነ ሁኔታ ማሰብም ሆነ መናገር አግባብነት ያለው ጉዳይ ነው። ነገር ግን አዎንታዊ ዐዋጅ፣ አዎንታዊ ውጤት፣ አሉታዊ ዐዋጅ ደግሞ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ዘላለማዊ የሆነ መንፈሳዊ ሕግ አለ ማለት ደግሞ ስሕተት ነው።

እግዚአብሔር እንዲባርከን በሙሉ ልብ መጸለይ አለብን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የምንጠይቀውን ነገር እንዲያደርግልን "ማዘዝ" አንችልም፤ ልናደርገውም አይገባም። ይህ ዐይነቱ ጸሎት ትሑት ሆነን፣ በአምላካችን በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ተደግፈን ጸሎታችንን እንዳናቀርብ ይከለክለናል። ምን ያህል ሰዎች በእምነት እንቅስቃሴ መምህራን የጸሎት ቀመር፣ "ያዘዙት ትእዛዝ" አልሞላ ብሎ፣ እግዚአብሔርን ተቀይመውት ይሆን?

በርካታ ሰዎች፣ "በእምነት ነው ትንቢት የተናገርነው፤ መገለጥ ያወረድነው" ሲሉ ይሰማል። እግዚአብሔር የሚናገሩትን ነገር ስለሰጣቸው ወይም መገለጥ ስላሳያቸው ሳይሆን፣ "አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ" (2ቆሮ 4÷13) ይሉናል (ልብ ይበሉ ይህ ክፍል፣ "አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ" የሚለው፣ የክርስቶስን ጌትነትና ትንሣኤ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን የምሥራች በመናገራችንም፣ ከፍተኛ ችግር እንዲሁም ስደት ደርሶብናል እያለ ነው)። ይህ፣ "አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ" የሚለው ቀመር የስንቶችን ትዳር እንዳፈረሰ፣ ስንቶችን ከሥራ እንዳፈናቀለ፣ አያሌ ሰዎች ጥሪታቸውን ሜዳ ላይ

እንዲበትኑ እንዳደረገ እንዲያው በአጠቃላይ ትውልድን እንዳወደመ ቢያንስ በቤተ ክርስቲያን የኖርን ሰዎች፣ በውል የምናውቀው ጉዳይ ነው። የችግሩ ሰለባ የሆኑም ወገኖች፣ “ጌታ እንዲህ ተናግሮኝ በቀኑ መጨረሻ እጄን አጨብጭቤ ባዶዬን ቀረሁ” በማለት በጌታ ላይ ልባቸው እጅግ ሲከብድ እንዲያውም አንዳንዶች ክርስትናን ላይመለሱበት ትተው ሲሄዱ ተመልክተናል።

ወገኖቼ ማንኛውም ትምህርት የራሱ ሆነ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት አለው። ይህ እኩይ ትምህርት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያመጣው ጥፋት፣ እንዲህ በቀላሉ ተነግሮ ተዘክሮ የሚያልቅ አይደለም። ምናልባትይም አስተምህሮ ያመጣው ውድመት ብቻ፣ የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ ጥናት የሚወጣው ድርሳን ይመስለኛል። ውድ ወገኖቼ ሰው አንድ ጊዜ ይሳሳታል፤ ምናልባትም ለተወሰነ ዓመት በስሕተቱ ውስጥ ሊቆይ ይችላል። ነገር ግን ዝንተ ዓለማችንን ልቡናችን እያወቀ በስሕተት ውስጥ ልንኖር አይገባም። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስ፣ “መታዘዛችሁ በተፈጸመ ጊዜ፣ አለመታዘዝን ሁሉ ለመቅጣት ተዘጋጅተናል” (2ቆሮ 10÷6) እንደሚለው፣ የትምህርቱን ማንነት በማጋለጥ መሠረተ እምነታችንን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ የትምህርቱን እኩይነት በማጋለጥ ክርስቲያኑንን ማኅበረሰብ ልንታደግ ይገባል። እግዚአብሔር አምላካችን በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን በኪነ ጥበቡ ይጠብቅ። እኛም የድርሻችንን ኀላፊነት መወጣት እንድንችል ጥበቡንና ኀይሉን ይስጠት። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።